# በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በክረምት መርሃ ግብር ለሚማሩ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች “የምርምር ዘዴ” በሚል ርእስ የተዘጋጀ የርቀት ትምህርት ሞጁል ግምገማ

**መንግስቱ ታደሰ**

*አህጽሮተ ጥናት*

*የዚህ ጥናት ዋና አላማ ለመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል የክረምት ተማሪዎች “የምርምር ዘዴ“ በሚል ርዕስ ተዘጋጅቶ የቀረበውን ሞጁል የተለያዩ ምሁራን ካቀረቧቸው ንድፈ ሀሳቦች አኳያ አዘገጃጀቱ ምን እንደሚመስል መገምገምና መተንተን ነው፡፡ የጥናቱ ዘዴ መሰረት ያደረገው በገባጭ የምርምር ዘዴ ውስጥ ተካቶ የሚገኘውን የይዘት ትንተና* (content analysis) *ስልትን ነው፡፡ በዚህ ስልትም በአላማው ስር የሚገኙ የምርምር ጥያቄዎችን ለመመለስ ያስችል ዘንድ የተለያዩ ምሁራን ያቀረቧቸውን መስፈርቶች መሰረት በማድረግ ለጥናት የተመረጠውን የርቀት ትምህርት ሞጁል ለመፈተሽ ተሞክሯል፡፡ የጥናቱ ውጤትም የሚያመለክተው ተማሪዎች ኮርሱን ተምረው ሲያጠናቅቁ ምን ሊያደርጉ እንደሚችሉ ባላወቁበት ሁኔታ ወደ ትምህርቱ እንደገቡ መደረጉ (አጠቃላይ አላማ አለመኖሩ) በሒሳም በኩል ዝርዝር አላማዎች በአብዛኛው ግልጽነት የጎደላቸው፣ በቀላሉ የማይለኩና ለትግበራ የሚያስቸግሩ ከመሆናቸውም ባሻገር ለዋለዋዊ ግድፈትም የበዛባቸው ናቸው፡፡ በሌላም በኩል ይዘቶቹ ቅደም ተከተላቸውን ያልጠበቁ እና መሰረታዊ የሆኑ የምርምር ጽንሰ ሀሳቦችን ከእነማብራሪያቸው ያላካተቱ እንዲሁም በመልመጃዎች፣ በተለያዩ ልምዶችና ማስረጃዎች ባለመደገፋቸው ተማሪዎችን በርቀት ለማስተማር የማስቻል አቅማቸው ዝቅተኛ መሆኑ ተስተውሏል፡፡ በመጨረሻም ተማሪዎች ለርቀት ትምህርት ተብሎ የተዘጋጀውን ሞጁል በሚያነቡበት ጊዜ ልምዱንና እውቀቱን ከቀረቡት ይዘቶች ጋር አጣምሮ፣ በምሳሌዎችና በማስረጃዎች እያስደገፈ የሚያስተምራቸው አካል እንዳለ እንዲሰማቸው አድርጎ ያለማቅረቡ ሁኔታ እንደ ሰፊ ክፍተት ታይቷል፡፡*

**ቁልፍ ቃላት፡-** የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት፤ የርቀት ትምህርት ሞጁል ግምገማ

## I. መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

የርቀት ትምህርት በኢትዮጵያ የቅርብ ጊዜ ክስተት ነው፡፡ Eshetu (2006) በጽሁፉ ላይ እንዳሰፈረው በ1950ዎቹ በተለያየ የስልጣን ቦታ ለሚገኙ የመንግስት ባለስልጣናት፣ ለፋብሪካ ሰራተኞችና ለወታደሮች የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በኢትዮጵያ እና በአሜሪካ ትብብር “የርቀት ትምህርት ለጎልማሶች” በሚል መርሃ ግብር ይሰጥ ነበር፡፡ ከዚያም በኋላ ትምህርቱ በቀድሞው የሀይለስላሴ ዩኒቨርሲቲ ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ከ1968-1972 ተግባራዊ ሲደረግ ቆይቷል፡፡ ከዚያም በኋላ የተወሰኑ አመታት ከተቋረጠ በኋላ እንደገና በትምህርት ሚኒስቴር ስር የጎልማሶች፣ የርቀትና ተከታታይ ትምህርት በ1978 ተጀመረ፡፡

የርቀት ትምህርቱም እንደዚህ እያለ ተጀምሮ በመንግስት ብቻ ይሰጥ የነበረው አድማሱን በማስፋት በተለያዩ የግል ተቋማት ከአንደኛ ደረጃ እስከ ከፍተኛ ትምህርት መሰጠቱን ቀጥሎ ዛሬ ላይ ደርሷል፡፡ በዚህም የመንግስትም ሆነ የግል ተቋማት የተማረ የሰው ኃይል በማፍራቱ ረገድ ያደረጉት እና በማድረግ ላይ ያሉት አስተዋጽኦ እንዲህ በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡

አንድ የርቀት ትምህርት ክፍል በተለያዩ የትምህርት ተቋማት በሚመሰረትበት ወቅት በቀዳሚነት የሚነሳው ጉዳይ የመማሪያ ሞጁሎች ዝግጅት ነው፡፡ ይህም በወቅቱ የተዘጋጀውን መርሃ ትምህረት መሰረት በማድረግ ከፍተኛ ልምድና እውቀት ባላቸው ምሁራን እንዲጻፉ ይደረጋል፡፡

የአንድን ሀገር የመማር ማስተማር እንቅስቃሴ ከግቡ ለማድረስ መማሪያ መጻህፎች ብቻ ሳይሆን የርቀት ትምህርት ሞጆሎችም ወሳኝነት አላቸው፡፡ ስለዚህ እነዚህ ሞጆሎች ከመዘጋጀታቸው በፊት ሊታሰብባቸው የሚገቡ ብዙ ጉዳዮች እንዳሉ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ በተለይ የርቀት ትምህርት ሞጁሎችን የሚያሰናዱ ምሁራን መርሃ ትምህርቱንም ሆነ ለክፍል ደረጃው የተዘጋጀውን መማሪያ መጽሃፍ መሰረት በማድረግ በሞጁሉ ውስጥ ሊካተቱ የሚገባቸውን ይዘቶች እንዴት ለይቶ ሳውጣቸው? እንዴትስ ሳደራጃቸው? በእንዴት ያለ የማስተማሪያ ዘዴስ ተጠቀሚ የተማሪዎችን የማንበብ ፍላጎት ሳነሳሳ? የሚሉ ጥያቄዎችን በአእምሯቸው ውስጥ በመያዝ በዝግጅቱ ወቅት መልስ ሊያገኙላቸው ይገባል፡፡

ነገርግን ሞጁሉን የሚያዘጋጁት ምሁራን በአብዛኛው በመደበኛው ትምህርት ተማሪዎችን ፊት ለፊት የሚያስተምሩ እንዲሁም በአብዛኛው የርቀት ትምህርት ኮርስ እንዴት እንደሚዘጋጅ በቂ እውቀት ያላገኙ በመሆናቸው የተማሪዎችን አላማ፣ አቅም፣ ፍላጎትና ተነሳሽነትን ባገናዘበ መልኩ የመጻፋቸው ሁኔታ የላላ ነው፡፡ ከፍተኛ ምርምር የሚያስፈልገው ቢሆንም በዚህ ምርምር የሚሰራውን ጨምሮ በመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በተለይም በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል ለርቀት ትምህርት ተብለው የሚዘጋጁ አብዛኛው የማስተማሪያ መጻህፍት አቀራረባቸው በተለመደው የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደት የተቃኘ መሆኑን ለተማሪዎች የማጠናከሪያ ትምህርት ለመስጠት እድሉን ባገኘሁበት ወቅት የታዘብኩት ጉዳይ ነው፡፡

በርቀት ትምህርት ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች በስራ የተወጠሩ፣ ከፍተኛ የቤተሰብና የማህበረሰቡን ሃላፊነት የተሸከሙ በመሆናቸው የሚዘጋጁላቸው የማስተማሪያ መሳሪያዎች ሳቢና በቀላሉ ሊረዷቸው የሚችሉ መሆን እንደሚገባቸው Holmberg (1981) በግለጽ ያስረዳሉ፡፡ በመሆኑም ፊት ለፊት በመደበኛው ትምህርት እንደምናስተምራቸው ተማሪዎች በተከታታይ ረጅም ማስታወሻ የምንሰጥበት ሳይሆን የመምህራንና የተለያዩ ምሁራንን ልምድ ያካተተ፣ በተለያዩ ምሳሌዎችና መልመጃዎች የታጀበ፣ የሚጻፍበት ቋንቋ ከተለያዩ ሰዋሰዋዊ ግድፈቶች የጸዳ፣ የአረፍተነገሮች እና የአንቀጾቹ አወራረድ ልክ እንደውሀ ጅረት የሚፈስ ሊሆን ይገባል፡፡

ስለዚህ ይህ ጥናት የሚያተኩርበት ሞጁል ያሉበት የአዘገጃጀት ችግሮች እና ጠንካራ ጎኖች ቢታወቁ የርቀት ትምህርት ማስተማሪያ መጽሀፎች እንደ አዲስ በሚዘጋጁበትም ሆነ በሚሻሻሉበት ወቅት ከፍተኛ ግብዓት እንደሚሆኑ አጥኚው ያምናል፡፡ በመሆኑም ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን እውነታዎች መሰረት በማድረግ እና ችግሮችን በተወሰነ መልኩ ለመፍታት ያስችል ዘንድ ይህ ጥናት ይጠና ዘንድ አነሳሽ ምክንያቶች ናቸው፡፡

## 1.2. የጥናቱ አላማ

የዚህ ወረቀት ዋና አላማ ለመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል የክረምት ተማሪዎች "የምርምር ዘዴ" በሚል ርዕስ ተዘጋጅቶ የቀረበውን ሞጁል የተለያዩ ምሁራን ካቀረቧቸው ንድፈ ሀሳቦች አኳያ አዘገጃጀቱ ምን እንደሚመስል መገምገም እና መተንተን ነው፡፡

በዚህ መሰረትም ጥናቱ ለሚከተሉት የምርምር ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣል፡፡

1. ለደረጃው የሚቀርቡት ዓላማዎች ተገቢነትና ግልጽነት ምን ያህል ነው?
2. የይዘቶች አደረጃጀት እና ተተግባሪነት እስከምን ድረስ ነው?
3. ቋንቋውና አቀራረቡ ተማሪዎችን የሚያነሳሳ ነው?

## 1.3 የጥናቱ አስፈላጊነት

በጥናቱ ዳራ ላይ እንደተጠቀሰው የርቀት ትምህርት ተማሪዎች በብዛት ጎልማሶች፣ በስራ የተጠመዱ፣ የተለያዩ ሀላፊነቶች ያሉባቸው ወዘተ. በመሆናቸው የሚዘጋጁት ሞጁሎች ለንባብ የሚያነሳሱ፣ ግልጽና በአግባቡ የተደራጁ ስሆኑ ይገባል፡፡ ይህ ሳይሆን ሲቀር ደግሞ በትምህርቱ ጥራት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማምጣቱ አይቀርም፡፡ ስለዚህም ጥናቱ የሚከተሉት ዋና ዋና ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡፡

1. አዲስ ለሚዘጋጁ የርቀት ትምህርት ሞጁሎች እንደ ግብዓት ያገለግላል፡፡
2. የርቀት ትምህርት ተቋማት የሚጠቀሙባቸውን የማስተማሪያ ሞጁሎች ድክመት እና ጥንካሬያቸውን በመፈተሽ ያሉባቸውን ችግሮች አስተካክለው እንዲጓዙ ያግዛል፤
3. ከዚህ በኋላ በስራ ላይ በዋሉ የተለያዩ የትምህርት መስኮች ለሚደረግ ሰፌ ጥናት እንደ መነሻ ሆኖ ያገለግላል፡፡

### 1.4 የጥናቱ ዘዴ

ጥናቱ መሰረት አድርጎ የተነሳው በገላጭ የምርምር ዘዴ ውስጥ ተካች የሚገኘውን የይዘት ትንተና (content analysis) ስልትን ነው፡፡ በዚህ ስልትም በአላማው ስር የሚገኙ የምርምር ጥያቄዎችን ለመመለስ ያስችል ዘንድ የተለያዩ ምሁራን ያቀረቧቸውን መስፈርቶች መሰረት በማድረግ ለጥናት የተመረጠው የርቀት ትምህርት ሞጁል ይተነተናል፤ ይገመገማል ፡፡

## II. የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት

### 2.1 የርቀት ትምህርት ምንነት

ስሙ እንደሚያመለክተው ከመደበኛው የፊት ለፊት የመማር ማስተማር ሂደት ወጣ ያለና ተማሪው ተዘጋጅቶ በሚሰጠው ሞጁል አማካኝነት ራሱን እያገዘ ትምህርት የሚያገኝበት ዘዴ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ይህንን ጉዳይ Holmberg (1981) ሲያጠናክረው የርቀት ትምህርት ተማሪና አስተማሪ በአካል በማይገናኙበት ሁኔታ የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም ተጽፈው በታተሙ እንዲሁም በኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች በመታገዝ ትምህርት ቤቶች ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች የመማር ማስተማሩን ሂደት የሚያከናውኑበት መሳሪያ ነው፡፡
የርቀት ትምህርት ግለሰባዊ ተግባራትን በከፍተኛ ሁኔታ የሚጠይቅ ሲሆን ተማሪው በአለው ትርፍ ጊዜ፡- ቤቱ ውስጥ፣ በጉዞ፣ በመዝናኛ ስፍራ፣ ወዘተ. ጥናቱን በማከናወን የሚማርበት ሂደት ነው፡፡ ይህም በማቀድ፣ ጊዜን ባግባቡ በመጠቀም ተማሪው እራሱን እንዴት መምራት እንዳለበት የሚለማመድበት ወቅት ነው፡፡

### 2.2 የርቀት ትምህርት ሞጁል ምንነት

የርቀት ትምህርት ሞጁሎች ለክፍል ደረጃው የተቀረጸውን መርሃ ትምህርት መሰረት በማድረግ ከመደበኛው የመማሪያ መጽሀፎች በተለየ መልኩ ትክክለኛና ኑባሬያዊ የጹህፍ መረጃዎችን፣ ታሪኮችን፣ በምሳሌና በበቂ ማስረጃዎች የተጠናከሩ ገለጻዎችን፣ በልዩ ልዩ ልምዶች የታጀቡ የሙከራና የምርምር ወጤቶችን ወዘተ. በማካተት እውቀትና ክህሎትን ለማዳበር እና የአንድን ሀገር የትምህርት ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ በሚያስችል ሁኔታ የተሰናዱ የማስተማሪያ መሳሪያዎች ናቸው፡፡

Allwright (1981) እንደሚገልጸው መማሪያ ሞጁሎች ተማሪዎች እንዲማሯቸው የተፈለጉት የትምህርት ይዘቶች፣ ማብራሪያዎች፣ መልመጃዎች፣ ፈተናዎች ወዘተ. ከተለያዩ ልምዶች ጋር አጣምረው በመያዝ ተማሪዎች ራሳቸውን

በራሳቸው ለመምራትና ለማስተማር የሚያስችሉ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ሞጁሎች ግልጽና በማያሻማ መልኩ በሚቀርቡ ማብራሪያዎች፣ ማጠቃለያዎች፣ በክለሳዎችና በተለያዩ ራስ ፈታሽ መልመጃዎች የተደራጁ ከመሆናቸውም በላይ በስእሎች፣ በፎቶ ግራፎች፣ በቻርቶች፣ በሰንጠረዦች የታገዙ መልእክቶችን ማስተላለፍ መቻል ይኖርባቸዋል፡፡ Rowntree (1981) እንደሚገልጸው በጽሁፍም ሆነ በምስል የሚቀርቡት ርእሰ ጉዳዮች ተማሪዎችን ለምርምር የሚጋብዙ ቢሆኑ ይመረጣል፡፡ ምክንያቱም በሞጁሉ ውስጥ የሚካተቱት ቁምነገሮች የተማሪዎችን የአስተሳሰብ አድማስ የሚያሰፉ፣ መልካም አመለካከትን የሚያጎለብቱ እንዲሁም ሌሎች አጋዥ መጽሀፎችን እንዲያነቡ የሚገፉፉ መሆን ስላለባቸው ነው፡፡

## 2.3 የርቀት ትምህርት ሞጁሎች ግምገማ እና አስፈላጊነት

አንድ የተሰራ ስራ ስተነሳለት አላማ ስኬት ላይ መድረስ አለመድረሱን የምናይበት ፣ የምናጠናበት፣ የምንመዝንበት መሳሪያ ግምገማ ሲባል እንደሚችል Hutchinson እና waters (1987) በግልጽ አስቀምጠዋል፡፡ የርቀት ትምህርት ሞጁሎች ግምገማም በዚህ ብያኔ ውስጥ አስገብተን መመልከት እንችላለን፡፡ ይኸውም ሞጁሉ ሲዘጋጅ የተቀረጸውን አላማ ለማሳካት የቀረቡት የትምህርት ይዘቶች፣ አቀራረቡ፣ ዘዴው፣ የተማሪውን ትኩረት መሳቡ፣ የቋንቋው ፍሰት ወዘተ. በግምገማው ወቅት የሚነሱ ነጥቦች ናቸው፡፡

የርቀት ትምህርት መማሪያ ሞጁሎችን ለመገምገም ስንነሳ የተለያዩ አላማዎችን ልንይዝ እንችላለን፡፡ የመጀመሪያው ሞጁሉ ተዘጋጅቶ ህትመት ከመግባቱ በፊት የታላሚዎችን ተማሪዎች አቅምና ችሎታ፣ የቀደመ እውቀት፣ አቀራረቡ እና ሌሎች መሰረታዊ ነገሮች ባግባቡ መካተት አለመካተታቸውን ለመፈተሽ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በስራ ላይ ያለን ሞጁል ድክመት ጥንካሬውን ለይቶ ለማውጣት እና ማስተካከያ ለማድረግ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ Smith (1999) እንደሚገልጸው የርቀት ትምህርት ኮርሶች ግምገማ በእያንዳንዱ ሂደት መከናወን አለበት ይላሉ፡፡ አያይዘው ሲገልጹም ግምገማው ሞጁሉ በሚዘጋጅበት ጊዜ፣ ወደ ህትመት ከመሄዱ በፊት፣ በትግበራ ወቅት እና ተማሪዎች ኮርሱን ወስደው ሲያጠናቅቁ የግምገማው ተግባር ሊሰራ ይችላል፡፡

Hutchinson (1987) እንደሚያስረዳው ግምገማ አጠቃላይ ግንዛቤን ከማስፋቱም በላይ የርቀት ትምህርት ሞጆሎች የተማሪዎችን የመማር ስልት ፈር እንዲያስይዙ፣ ትምህርቱን በተቀናጀ እና ጥራት ባለው መልኩ እንዲማሩት፣ በተሳሳተ መልኩ የቀረቡ የትምህርት ይዘቶች እንዳይካተቱ እንደዚሁም አጋዥ መጻህፍትንና አሀዶችን በተገቢው ቦታ እንዲገለገሉ ይረዳል ብሏል፡፡

## 2.4 የርቀት ትምህርት ሞጁሎች እንዴት ይገመገማሉ?

ከዚህ በፊት ለመጥቀስ እንደተሞከረው መማሪያ ሞጁሎች ለአገልግሎት ከመዋላቸው በፊት፣ በአገልግሎት ላይ እያሉ እና ከአገልግሎት ውጭ ሆነው ሲገመገሙ ይችላሉ፡፡ በዚህም ምክንያት የማስተማሪያ መሳሪያዎች በተለያየ መንገድ ሲገመገሙ እንደሚችሉ የተለያዩ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ ለምሳሌ McDonough and Shaw (1913) ውጫዊ ግምገማ (ሽፋኑን፣ መግቢያውን፣ ማውጫውን ወዘተ. የምመለከትበት)፣ ውስጣዊ ግምገማ (ይዘቶቹ ውስጣዊ አደረጃጀት፣ ዝምድና፣ ተያያዥነታቸው፣ ተለጣጣቂነታቸው፣ ደረጃ ጠባቂነታቸው ወዘተ.) እና ጠቅላላ ግምገማ (ከመርሃ ትምህርቱ ጋር ያለው ዝምድና) ብለው በሶስት በመክፈል አስቀምጠዋቸዋል፡፡

በዚህ የምርምር ስራ ውስጥ ካለው የጊዜ እና የማቴሪያል ጥበት አኳያ አላማዎችን ለማሳካት ያስችላሉ ተብለው በታሰቡት (በይበልጥ ከይዘታዊ ግምገማ ጋር የሚዛመዱ) የመገምገሚያ መስፈርቶችን በመጠቀም ለመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተዘጋጀውን “የምርምር ዘዴ” የሚለውን ሞጁል ለመገምገም ተሞክሯል፡፡

### 2.4.1 የርቀት ትምህርት ሞጁሎች አላማ

የርቀት ትምህርት ተማሪዎች ስራቸውን በተገቢው መንገድ ለማከናወን ያመቻቸው ዘንድ በአላማዎች ላይ ግልጽ የሆኑ ሀሳቦችን እንደሚፈልጉ Holmberg (1981) ይገልጻሉ፡፡ ይህም በደረጃው ለተዘጋጀው ሞጁል የሚቀርቡት አላማዎች ተገቢነትና ግልጽነት ኖሯቸው የትምህርቱን መነሻ እና መድረሻ የሚጠቁሙ እንዲሁም ኮርሱን ሲያጠናቅቁ ምን ምን ቁምነገሮችን እንደሚሰሩ ወይም እንደሚያከናውኑ በሞጁሉ መግቢያ እና በየምእራፎች መጀመሪያ ላይ ሲሰፍሩ ይገባል፡፡ ስለዚህ አላማዎች ሲቀረጹ መስተጋብራዊ እና በተቻለ መጠንም ተማሪዎች በቀላሉ ሲረዷቸው በሚችል መልኩ መቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡ በተጨማሪም፡-

- ተማሪዎች የሚማሯቸውን ጽንሰ ሀሳቦች መሰረት ያደረጉ፣
- ተማሪዎች ሲያውቋቸው የሚገቡ ክሂሎችን ያካተቱ፣
- ከተማሪዎች የቀደመ እውቀት፣ ልምድ እና ማህበራዊ ሁኔታ አኳያ ተገናዝበው የተቀረጹ፣
- በቀላሉ ሲለኩና ሲተገበሩ የሚችሉ፣
- የተመረጡትን ይዘቶች በአግባቡ የሚያንጸባርቁ
- ችግር ፈቺ ስልቶችን ያካተቱ እና
- ከሰዋሰዋዊ ግድፈት የጸዱ መሆን አለባቸው፡፡

### 2.4.2 የርቀት ትምህርት ሞጁሎች ይዘት

በመማሪያ ሞጁሉ ውስጥ ተካተው የሚቀርቡ ይዘቶች ሲቀርቡና ሲደራጁ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያሻቸዋል፡፡ ይዘቶች የተሰናዳውን አላማ ለማሳካት ይችሉ ዘንድ ተፈትሸውና ተመርምረው ለደረጃው በሚመጥን መልኩ ሲመረጡ ይገባል፡፡ ምክንያቱም ከርዕሱ ጋር የተያያዘው ማንኛውም ጽሁፍ ለማስተማሪያነት አያገለግልምና፡፡ ስለዚህ ይዘቶቹ ሲመረጡና ሲደራጁ፡-

- ሲሰጥ ከታሰበው ትምህርት አላማ ጋር የተዛመዱ፣
- የተማሪዎችን እውቀት በተግባር ላይ የማዋል ብቃት የሚያዳብሩ፣
- በቅደም ተከተል፣ በተገቢ መጠንና በምዕራፍ ተከፋፍለው ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከተጨባጩ ወደ ረቂቁ፣ ከሚታወቀው ወደ ማይታወቀው የተደራጁ፣
- የተማሪዎችን እውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት በተመጣጣኝ ሁኔታ የሚያስጨብጡ፣ በሞጁሉ ውስጥ የተካተቱ ሰንጠረዦች፣ ዲያግራሞች፣ ስእሎች ወዘተ. ግልጽና ማራኪ የሆኑ፣
- ለደረጃው የሚመጥኑ እና የተማሪውን እድሜ፣ የትምህርት ደረጃ፣ ልምድ ወዘተ. ያገናዘቡ እና
- ይዘቶቹ ከጽንሰ ሀሳብ እና ከሰዋሰዋዊ ግድፈቶች የጸዱ መሆን አለባቸው፡፡

### 2.4.3 የርቀት ትምህርት ሞጁሎች ቋንቋና አቀራረብ

የርቀት ትምህርት ውስጣዊ ይዘት ከመማሪያ መጽሃፎች በአብዛኛው የተለየ አቀራረብ አለው፡፡ ምክንያቱም ሞጁሎቹን ከቅርብ ሆኖ የሚመራ እና የሚያስተምር በመደበኛነት የተመደበለት አካል ባለመኖሩ ነው Holmberg (1981)፡፡ በመሆኑም ተማሪው ትምህርት የሚሰጠው፣ የሚደግፈው፣ የሚመራው፣ ልምዶቹን የሚያካፍለው፣ ምግበ መረጃ የሚሰጠው ሰው በውስጠ ታዋቂነት እንዳለ አድርጎ እስከሚቆጥር ድረስ ግልጽና ተጠየቃዊ አካሄድ በተሞላበት መልኩ ቀለል

ባሉ ቋንቋዎች ትምህርቱ ሊቀርብለት ይገባል፡፡ Dodds (1983) ይህን ሲያጠናክር ተማሪዎች ሞጁሉን በሚያነቡበት ጊዜ ለችገራቸው ነገር አፋጣኝ ምላሽ የማያገኙ፣ የሚያበረታታቸው እና ልምዱን የሚያካፍላቸው የሌለ በመሆኑ ዝግጅቱ እና አቀራረቡ ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግለት እንደሚገባ ሳይጠቁም አላለፈም፡፡

ከዚህም ሌላ ተማሪው በግሉ እንዲመራመር፣ እንዲጠይቅ፣ ችግሮችን እንዲፈታ እና የማንበብ ፍላጎቱ እንዲነሳሳ የማድረግ ኃይል ያለው አቀራረብ ወሳኝነት አለው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከንድፈ ሀሳብ ትምህርት በኋላ ያሉ ልምምዶችም ሆነ መልመጃዎች በተግባር ላይ እንዲውሉ እና የተማሪውን ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቁ ሆነው መደራጀትና መቅረብ ይኖርባቸዋል (cunningsworth, 1984)፡፡

በሌላም በኩል እንደ Nuttal (1996) ገለጻ ለደረጃው የቀረቡት መማሪያዎች አሻሚ ከሆኑ እና ከበድ ካሉ ቃላት የጸዱ፣ ውስብስብነት ያላቸውን የሰዋሰው መዋቅሮች ያስወገዱ መሆን እንዳለባቸው አስረድቷል፡፡ ይህም በአቀራረቡ ውስጥ አረፍተ ነገሮቹ ያልረዘሙ እና የባለቤትና የግስ አስመጣጣም የማይስተዋልባቸው፣ በአንቀጹ ውስጥ የሚገኙ አረፍተ ነገሮች እርስ በርስ የተሳሰሩ እና ወደ አንድ ዋና ሀሳብ የሚያመሩ፣ የአጻጻፍ ስልቱም ፍሰት ኖሮት የተማሪውን የማንበብ ፍላጎት የሚያነሳሳ እና የሚያስደስት መሆኑን ማስተዋል ያስፈልጋል፡፡

## III. የይዘት ትንተናና ግምገማ

### 3.1 የርቀት ትምህርቱ ሞጁል የውጭ ሽፋን

በኮርሱ ውስጥ የሚገኙትን መግቢያዎች በዝርዝር ከመፈተሻችን በፊት የውጭ ሽፋኑ ምን እንደሚመስል እንመልከት፡፡

**የምርምር ዘዴዎች**
**(Research Methods)**
**(ELAM 403)**

**ሞጁል**

**2002 ዓ.ም**

የውጭ ሽፋኑን ስንመለከት ለየትኞቹ ተማሪዎች እንደተዘጋጀ፣ ያዘጋጀው ተቋም ማን እንደሆነ፣ ያለው የክፊዲት መጠን ስንት እንደሆነ የሚያመላክት ነገር የለውም፡፡ በመሆኑም ይህን ሞጁል አግኝቶ ለማንበብ የሚሞክር ሰው ኮርሱን ለእነማን የተዘጋጀ ነው? የርቀት ትምህርት ነው ወይስ? የሚሉ ጥያቄዎችን ማንሳቱ አይቀርም፡፡

### 3.2 የርቀት ትምህርቱ ሞጁል መግቢያ

#### 3.2.1 የርቀት ትምህርቱ ሞጁል አጠቃላይ መግቢያን በተመለከተ

የርቀት ትምህርት ኮርስ አዘጋጆች በኮርሱ መግቢያ ላይ በውስጡ የተካተቱት ይዘቶች፣ ምሳሌዎች፣ መልመጃዎች፣ ፈተናዎችና የተለያዩ ተግባራት እንዴት ሊከናወኑ እንደሚችሉ ጥርት ባለ መልኩ ማቅረብ አለባቸው፡፡ ተማሪው ወደ ትምህርቱ ዘልቆ ከመግባቱ በፊት ምን ምን ተግባራትን ማከናወን እንዳለበት፣ በውስጡ የሚገኙ ይዘቶች ምን እንደሚመስሉ፣ ኮርሱን ሲያጠናቅቅ ከእሱ ልምድና ገጠመኝ ጋር አጣምሮ በትምህርት ላይ እያለም ሆነ ወደ ስራ ሲሰማራ ሊሰራበት የሚችለውን ነገር ማመላከት ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም ኮርሱን ለማጠናቀቅ የሚፈጅበትን ጊዜ፣ እንዴት ማንበብ እንዳለበት፣ እንዴት እንደሚመዘን እና ሊያነባቸው የሚገቡ አጋዥ መጻህፍችን በአጠቃላይ መግቢያው ላይ ማሳወቅ ለትምህርቱ ያለውን

ዝግጁነትና ተነሳሽነት የበለጠ ያጠናክረዋል፡፡ ነገር ግን “የምርምር ዘዴ” የሚለው ኮርስ አጠቃላይ መግቢያ የሌለው በመሆኑ ከላይ በዘረዘርናቸው መስፈርቶች መገምገም አልተቻለም፡፡

### 3.2.2 የርቀት ትምህርት ሞጁሉ የምዕራፎች መግቢያ

| መግቢያ | የመግቢያው አጻጻፍ |
|---|---|
| የምዕራፍ አንድ መግቢያ | በሁለት አረፍተነገሮች የተጠናቀቀ ሲሆን ተማሪው ወደ ምዕራፉ ይዘቶች እንዲገባ የሚያነሳሳና ወደ ውስጥም ገብቶ እንዲያነብ ጉጉትን የሚጭር አይደለም፡፡ |
| የምዕራፍ ሁለት መግቢያ | መግቢያው የትምህርቱን ዋና ዋና ርዕሰ ጉዳዮች የሚያስቀምጥ እንጅ ያለፈውን ምዕራፍ ካሁኑ ጋር እያተሳሰረ ተማሪዎች ወደ እለቱ ትምህርት እንዲገቡ የሚያነሳሳ አይደለም፡፡ |
| የምዕራፍ ሶስት መግቢያ | መግቢያ የለውም |
| የምዕራፍ አራት መግቢያ | መግቢያው ከዚህ በፊት ከነበሩት ምዕራፎች በተለየ መልኩ ሰፋ ያለና የተብራራ ነው፡፡ በውስጡም ወደፊት ሲማሩቸው የሚገቡትን ይዘቶች ያሳየ እና በማጠቃለያ መልክም የቀረበ ነው፡፡ ነገር ግን ከዚህ በፊት የቀረበውን ምዕራፍ ካሁኑ ጋር ያለውን ግንኙነት ለማሳየት አልሞከረም፡፡ |
| የምዕራፍ አምስት መግቢያ | መግቢያው ባንጻራዊነት ከዚህ በፊት የነበሩትን ምዕራፎች ካሁኑ ጋር አዛምዶ ያቀረበ በመሆኑ የተሻለ ነው ማለት ይቻላል፡፡ |

ባጠቃላይ በሁሉም ምዕራፎች ውስጥ ተማሪው በስሩ የቀረቡትን ይዘቶች ከባለፈው ጋር ያላቸው ግንኙነት ምን እንደሚመስል እና እያነበበም ሆነ ከማንበቡ በፊት ምን ማድረግ እንዳለበት የሚጠቁም እንዲሁም መልመጃዎችን እንዴት እንደሚሰራና እንዴት እንደሚመዘን የሚያመላክት ነገር የለውም፡፡

## 3.3 የርቀት ትምህርት ሞጁሉ አላማ

### 3.3.1. የኮርሱን አጠቃላይ አላማ በተመለከተ

Holmberg (1981) እንደሚያስረዱት ተማሪዎች ወደ ኮርሱ ጠልቀው ከመግባታቸው በፊት የሞጁሉን አጠቃላይ አላማዎች ማለትም ትምህርቱን ሲያጠናቅቁ ምን ምን ነገሮችን በቃል፣ በጽሁፍ፣ በዘገባ፣ እንዲሁም በተግባር ሲያከናውኑ እንደሚችሉ በግልጽ ማወቅ አለባቸው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች ለኮርሱ ገንዘባቸውን፣ ጊዜያቸውን መስዋዕት ለማድረግ ሲወስኑ “ይህን ተምሬ ይህን እሰራለሁ” የሚል የራሳቸው ግብ አላቸው፤ በመሆኑም የተቀረጸው አላማ ከእነሱ ጋር መጣጣም አለመጣጣሙን ያረጋግጣሉ፡፡
ነገር ግን “የምርምር ዘዴ” በሚል ርዕስ የተዘጋጀው የርቀት ትምህርት ሚጁል ገና ሲጀመር አጠቃላይ አላማ የለውም፡፡ ተማሪው ትምህርቱን የሚማረው ለምንድን ነው? ኮርሱን ሲያጠናቅቅ በተማሪው ኮርስ ምን ምን ነገሮችን ያከናውናል? የሚሉት መሰረታዊ ጥያቄዎች በግልጽና በማያሻማ ሁኔታ ካልተቀመጡ ተማሪው መነሻ እና መድረሻውን ለማወቅ ይቸገራል፡፡ በውስጡም የተካተቱት ይዘቶች፣ መልመጃዎች፣ ፈተናዎች፣ እና የተለያዩ ተግባራት የመጨረሻ ግባቸው አጠቃላይ አላማውን ማስፈጸም ነው፡፡ ስለዚህ ሞጁሉ በሚዘጋጅበት ወቅት ወደ መጨረሻው ውጤት ሲያደርሱ የሚያስችሉትን እነዚህን አላማዎች ባግባቡ ማስፈር ለተማሪው አቅጣጫ በማሳየቱ ረገድ ያለውን ትልቅ አስተዋጽኦ አዘጋጆች መዘንጋት የለባቸውም፡፡

### 3.3.2 በኮርሱ ምዕራፎች የሰፈሩትን ልምምዶች በተመለከተ

በኮርሱ ውስጥ ከሰፈሩት አምስት ምዕራፎች መካከል በሶስቱ ላይ ብቻ ትንተናውና ገለጻው ይከናወናል፡፡ ግምገማ የሚደረግባቸው ምዕራፎችም፡- አንድ፣ ሁለት እና አምስት ናቸው፡፡

#### 3.3.2.1 የምዕራፍ አንድ ልምምዶች

"የምርምር ምንነትና አይነቶች" በሚል ርእስ ውስጥ የቀረቡት አራት ልምምዶች የአጻጻፍ፣ የአገላለጽ፣ የአተገባበር ችግሮች እንዳሉባቸው በቀላሉ መመልከት ይቻላል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ለማሳያ ያክል ሁለቱን ብቻ እንመለከታለን፡፡

1. "የምርምር ምንነትና ተግባር በዝርዝር ትናገራላችሁ፡፡"

ይህ ልምምድ ግልጽነት የሌለውና ተማሪዎችም በቀላሉ ሊተገብሩት የሚያዳግታቸው ነው፡፡ ምክንያቱም ምርምር በራሱ ሰፊ ጽንሰ ሀሳብ ነው፤ በውስጡም የተለያዩ ክፍሎችን አካቶ ይይዛል፤ ከእነዚህም መካከል፡- ትምህርታዊ፣ ድርጊታዊ፣ ተግባራዊ፣ አይነታዊ፣ አሃዛዊ ምርምር ወዘተ. ይገኙበታል፡፡ ምርምር የሚለው አጠቃላይ ጽንሰ ሀሳብ የራሱ የሆነ ጥቅል ብያኔ ሲኖረው ሌሎች ደግሞ እንደ አይነታቸው ምንነታቸውም ይለያያል፡፡ በዚህም የተነሳ ተማሪው ግራ መጋባቱ አይቀርም፡፡ ዓላማ የሚነነበውን ይዘት የማመላከት፣ አቅጣጫ የመጠቆም፣ ሊያሳካ የሚፈልገውንም ጉዳይ በማያሻማ እና ጥርት ባለ መልኩ ሊያቀርብ ይገባል፡፡

በሌላም በኩል በአንድ ልምምድ ውስጥ ሁለት ጉዳዮች መስፈር እንደሌለባቸው ብዙ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ ከላይ በተጠቀሰው ልምምድ ውስጥ የሚስተዋለው ግን የዚህ ተቃራኒ ነው፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን ተማሪዎች የምርምርን ተግባር ለመግለጽ የሚያስችላቸው ፍፊ ነገር በሞጁሉ ውስጥ በግልጽ የሰፈረ ነገር የለም፡፡ Graves (1996) አንድ የማስተማሪያ ጽሁፍ በሚዘጋጅበት ጊዜ ወደ መጨረሻ ውጤት ሊያደርሱ የሚያስችሉትን እቅዶች እና ይዘቶችን መመርመርና ወደ ታላሚው ግብ ለመድረስ የተለያዩ ነጥቦችን ማሰብ ተገቢ እንደሆነ በግልጽ አስረድቷል፡፡

በተጨማሪም በራሱ ለዋለዋዊ ግድፈት ያለበት በመሆኑ ለማንበብ በሚሞከርበት ጊዜ ያነቀፋል፡፡ ይኸውም ተሳቢ አመልካቿ "ን" ባለመኖሯ ምክንያት አረፍተ ነገሩ ሙሉ ስሜት አይሰጥም፡፡ ሲስተካከልም "የምርምርን ምንነትና ተግባር በዝርዝር ትናገራላችሁ" ይሆናል፡፡ ከዚህም ሌላ "ትናገራላችሁ" የሚለው ቃል በተግባር ሂደት ውስጥ ለመለካትና ለመመዘን አስቸጋሪ ነው፡፡ ስለሆነም ምንነቱን እና ተግባሩን ከመናገር ይልቅ በመግለጽ ወይም በማስረዳት ቢተካ የተሻለ ነው፡፡

2. "የሳይንሳዊ ምርምር አሰራ አንዱን ባህሪያት በትክክል ትዘረዘራላችሁ፡፡"

ለመሆኑ ሳይንሳዊ ምርምር ምንድን ነው? ሳይንሳዊ ያልሆነውስ? በሞጁሉ ውስጥ ምንም የተሰጠ ማብራሪያ ባለመኖሩ ምክንያት ልምማውን ተግባራዊ ለማድረግ አዳጋች ነው፡፡ እንደዚሁም ከዚህ በላይ ከቀረበው ልምምድ ጋር ስናስተያየው አሻሚነት አለው፡፡ ይህ ጉዳይም ምርምር ሰፋ ያለ ጽንሰ ሀሳብ ያለው መሆኑን በግልጽ ያሳዮናል፡፡

በሌላም በኩል አስራ አንድ የተባሉት የምርምር ሳይንሳዊ ባህሪያት ከ Best (1981) "ምርምር በትምህርት ውስጥ" በሚል ርዕሰ ጉዳይ ከቀረበ መጽሀፍ የተወሰዱ ናቸው፡፡ መጽሃፉም ምርምር አንድ ወጥ ብያኔ የሌለው በመሆኑ ባህሪያቱንና አስፈላጊነቱን በማብራራት አንባቢዎች ግንዛቤያቸውን እንዲያሰፉ ያሰፈረው እንጂ በዚህ ሞጁል እንደተጠቀሰው የሳይንሳዊ ምርምር ባህሪያት ተብሎ የተቀመጠ አይደለም፡፡ በተጨማሪም በቁጥር ወሰኖና ተማሪዎችም ምንም ሳያዛንፉ "በትክክል" አስራ አንዱንም እንዲያስቀምጡ ብሎ ልምማ መቅረጽ ተማሪዎችን ለሽምደዳ መዳረግ ወይም ማስጨነቅ ነው፡፡ ይህ ልምማም ይቀመጥ ከተባለ " የምርምርን ባህሪያት ትገልጻላችሁ" ተብሎ ቢቀመጥ የተሻለ ነው፡፡

በአጠቃላይ አሳማው ከሰዋሰዋዊ ግድፈት በተጨማሪ ( የሳይንሳዊ ምርምርን አስራ አንድ ባህሪያት… መባል ሲገባው…) ግልጽነት የጎደለውና ተተግባሪነቱም ችግር ያለበት ነው፡፡

### 3.3.2.2 የምዕራፍ ሁለት አላማዎች

“የምርምር ዘዴዎች” በሚል ርዕሰ ስር በምዕራፉ የቀረቡት አላማዎች ሶስት ሲሆኑ አሻሚ የሆኑና እና ተተግባሪነትም የጎደላቸው ናቸው፡፡ እንደሚከተለው በዝርዝር ይቀርባሉ፡፡

1. “የምርምር ዘዴዎችንና ስልቶችን ትለያላችሁ፡፡”

ይህ አላማ ሁለት ለብያኔ የሚያስቸግሩ አሻሚ ቃላትን በውስጡ አካቶ ይዟል፡፡ እነሱም ዘዴ እና ስልት ናቸው፤ ስለሆኑ እነዚህ ቃላት በምን ይለያያሉ? በምንስ ይመሳሰላሉ? ለሚሉት ጥያቄዎች በሞጁሉ ወስጥ ምንም የተጠቀሰ ነገር የለም፡፡ እንዲያውም ሁለቱን ጽንሰ ሀሳቦች ተመሳሳይ አድርጎ ይወስዳቸዋል፡፡ እንደ Rechards and Rodgers (2001) ገለጻ ስልቶች በዘዴ ውስጥ የሚገኙ እና ጠበብ ያለ ጽንሰሀሳብ ያላቸው መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ ነገርግን በሞጁሉ ውስጥ በሰፈረው ኣላማ ላይ ሁለት የተለያዩ ነገሮች ተደርገው ከተቀረጹ በኋላ ወደ ይዘቱ ስንመጣ ደግሞ አንድ አይነት ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ስለዚህ አላማውና ይዘቱ ተመጋጋቢ ባለመሆናቸው የተነሳ አደናጋሪነታቸው ከፍተኛ ነው፡፡ ተማሪዎች አላማውን በሚያነቡበት ወቅት አሻሚ የሆኑ ቃላት ሲገጥሟቸው ተገቢውን መልዕክት በተገቢው መንገድ ስለጨበጥ ይቸገራሉ፤ ወደፊት እንደርስበታለን ብለው የሚያስቡትን ግብ ለማሳካትም አዳጋች ይሆንባቸዋል፡፡

2. “የምርምር ርዕስ ትመርጣላችሁ፡፡”

የምርምር ርእሶች አይነታዊ ወይም አሃዛዊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ እንደ ጥናቱ ችግር አይነት በታሪካዊ፣ በገላጭ፣ በሙከራዊ የምርምር ዘዴዎች ይቃኛሉ፡፡ በዚህ ሞጁል የቀረበው አላማ የተማሪዎችን ልምድና የእውቀት ደረጃ ባገናዘበ መልኩ ርእሳቸውን የሚመርጡት በየትኛው የምርምር አይነትና ዘዴ ነው? የምርምር ርዕሰ ጉዳይ የሚመርጡትስ በዚህ ምዕራፍ ነው ወይስ? የሚሉ ጥያቄዎችን የሚያስነሳ በመሆኑ ግልጽነት ይጎድለዋል፡፡

በሌላም በኩል ከዚህ ቀጥሎ በሚነሳው ግምገማ ላይ የሚቀርብ ቢሆንም የሞጁሉን ውስጣዊ ይዘት በምንመለከትበት ጊዜ፡- የምርምር ችግር ምንድን ነው? ችግሮች የት ይገኛሉ? የምርምር ችግር አመራረጥና ማብራሪያ? ችግሮቹ ወደ ርእስነት እንዴት ይቀየራሉ? የሚሉት ቁልፍ ጥያቄዎች ባልተገለጹበት ሁኔታ “የምርምር ርዕስ መምረጥን” እንደ ዓላማ መቅረጽ ተገቢነት የለውም፤ ተተግባሪም አይደለም፡፡ ይህ አላማም መቀመጥ ካለበት በጥናቱ ንድፍ (research proposal) (በዚህ ሞጁልም ባልተለመደ ሁኔታ መጨረሻ ላይ ገብቷል) በሚለው ምዕራፍ ውስጥ ነበር፡፡

3. “የምርምር ስራዎችን ትገመግማላችሁ፡፡”

አንድ ተማሪ የምርምር አይነትና ዘዴዎችን ብቻ ተምሮ የምርምር ስራዎችን እንዴት ይገመግማል? ይህንን ተግባር ማከናወንስ በዚህ ደረጃ የሚታሰብ ነው? ይህን አላማ ለማሳካት ያመች ዘንድስ በሞጁሉ ውስጥ የምርምር ስራዎች እንዴት እንደሚገመገሙ በማስረጃ የተደገፈ ገለጻ ተደርጓል? የሚሉ ጥያቄዎች ቢነሱ መልሳቸው አሉታዊ ነው፡፡

በመሆኑም በቅድሚያ በምርምር ውስጥ የሚካተቱ ፍሬ ነገሮችን ከእነአተገባበራቸው ማብራሪያ መስጠት፣ ቀጥሎም የምርምር ንድፍ እንዴት እንደሚሰራ ማሳየት፣ በመጨረሻም የዋናውን ጥናት ቀርጽ እና ይዘት ምን

እንደሚመስል በመግለጽ ወደ ምርምር ስራው ማስገባት ሲቻል ዘለው ወደ ምርምር ስራዎች ግምገማ እንዲገቡ ታሳቢ አድርጎ አሳማ መንደፍ ተገቢነት የለውም፡፡

#### 3.3.2.3.የምዕራፍ ሶስት አላማዎች

የምዕራፍ ሶስት አላማዎች አምስት ሲሆኑ ሶስቱ በተነጻጻሪነት ሊለኩ እና ሊተገበሩ የሚችሉ ናቸው፡፡ ነገር ግን በአራተኛ እና በአምስተኛ ደረጃ የተቀመጡት አላማዎች ይተገበሩ ዘንድ በሞጁሉ ውስጥ ግልጽና አላማኝ ማብራሪያ አልተሰጣቸውም፡፡ ሁለቱ አላማዎችም የሚሳኩት እያንዳንዱ ተማሪ የዶ/ር ያለው እንዳወቀን "የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበራቸው" የሚለውን መጽሃፍ ሲያገኝ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የሚታሰብ አይደለም፡፡ "የምርምር ተዛማጅ ጽሁፎች ክለሳ አጻጻፍ" በሚል ርዕስ ስር የተቀመጡት አላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የተዛማጅና የዋቢ ምንጮችን አጠቃቀስ ዘዴዎች በዝርዝር በትክክል ትጽፋላችሁ፡፡
- የአሜሪካን የስነባህሪ ባለሙያዎች አጻጻፍ ቅርጽን በመከተል ዋቢ ምንጮችን   ትጽፋላችሁ፡፡

በምርምር ጽሁፍ ውስጥም ሆነ በዋቢ ጽሁፎች ላይ የምንጮች አጠቃቀስ ተጨማሪ ምርምር ቢያስፈልገውም ለመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪዎች ብቻ ሳይሆን ለሁለተኛና ለሶስተኛ ዲግሪ ተማሪዎችም የአተገባበሩ ጉዳይ አነጋጋሪ ነው፡፡ የሀርቫርድ፣ የብሪቲሽ መደበኛ፣ የአሜሪካ ስነ ባህሪ ባለሙያዎች ማህበር፣ የቺካጎ፣ ኤም ኤል ኤ፣ ወዘተ. የአጠቃቀስ ስርአቶች ወሰብሰብ ያሉና ብዙ ንባብን የሚጠይቁ ናቸው፡፡ ስለዚህ ተጨማሪ ንባብ ኢንዲያደርጉ ማበረታታት እንዳለ ሆኖ ለዚህ ደረጃ በሚመጥን መልኩ ቀለል አድርጎ ከተለያዩ ምሳሌዎችና ማስረጃዎች ጋር በማስተሳሰር በሞጁሉ ውስጥ ማቅረብ ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡ አለበለዚያ አላማውን ለመተግበር ያስቸግራል፡፡

#### 3.3.2.4 የምዕራፍ አራት አላማዎች

በዚህ ምዕራፍ ስር የተቀመጡ አላማዎች የተጻፉባቸው አረፍተነገሮች ሰዋሰዋዊ ግድፈት ያለባቸው በመሆኑ ተማሪዎች አንብበው ምልዕክቱን በአግባቡ ይጨብጣሉ ተብሎ አይታሰብም፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን የተቀመጡት የምርምር ጽንሰ ሀሳቦች ግልጽነት የጎደላቸውና አሻሚም ከመሆናቸው በተጨማሪ ይዘቱ ሳይኖር አላማም የተቀረጸበት ሁኔታም አለ፡፡ ለምሳሌ "በጥናት ንድፋችሁ ጊዜ የጥናቱን ክፍሎችና አሳባዊያንን በትክክል ትነድፋላችሁ፡፡" የሚለው አላማ ተማሪዎች የምርምር ንድፍ ምንነትን፣ ጠቀሜታ እና በውስጡ የሚካተቱትን ቁምነገሮች በዝርዝር ሳይማሩ እንዴት ተግባራዊ ሊሆን ይችላል? ስለ "ጥናት ንድፍ አጻጻፍ ቢጋር" በሚል ንዑስ ርዕስ ባጭሩ የተገለጸውም በምዕራፍ አምስት ላይ ነው፡፡ የጥናት ንድፍ የሚለው የምርምር መሰረታዊ ጽንሰ ሀሳብ በምእራፉ መጨረሻ ላይ ሳይሆን የምርምር አይነትና ዘዴዎችን ከተማሩ በኋላ ቢሆን ይመረጣል፡፡ የምርምር ክፍሎችና አሳባዊያን አጻጻፍ በሚለው ርዕስ ስር የተቀመጡት አላማዎች ለማስረጃነት ያህል የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የጥናት ዋና ዋና ክፍሎችን በትክክል ትጽፋላችሁ፡
- በእያንዳንዱ የጥናት ክፍል ውስጥ አስፈላጊ የሚባሉትን አሳባዊያን ትጽፋላችሁ፡፡
- በጥናት ንድፋችሁ ጊዜ የጥናቱን ክፍሎችና አሳባዊያንን በትክክል ትነድፋላችሁ፡፡
- የጥናታችሁን መጠይቆች መመሪያዎችን በምንበብ በትክክል ታዘጋጃላችሁ፡፡
- የመረጃ ውጤቶች አደረጃጀት በትክክል ካደራጃችሁ በኋላ ትተነትናላችሁ፡፡
- የጥረ ተመራማሪ ተግባራትን እና ስነምግባሮችን በመለየት በተግባር ታሳያላችሁ፡

### 3.3.2.5 የምዕራፍ አምስት አላማዎች

ምዕራፉ “የምርምር አጻጻፍ ቢጋር” በሚል ርእስ የቀረበ ሲሆን አላማዎቹ የተቀረጹትም እንደ ማጠቃለያ ከዚህ በፊት የተማራችሁትን ትምህርት እንዲያስታውሱ በማሰብ ነው፡፡አላማዎቹም የግልጽነት ችግር ያለባቸው ናቸው፡፡ እንደሚከተለው ይቀርባሉ፡፡

- በምርምር ንድፍና የመጨረሻ ስራ አጻጻፍ ያለውን የቀርጽ ልዩነት ትናገራላችሁ፡፡
- በምርምር ንድፍና በመጨረሻው ስራ የሚካተቱትን ክፍሎችና አላባዊያን ትለያላችሁ፡፡
- የጥናታችሁን ንድፍ የምርምር ስራችሁን ከመጀመራችሁ በፊት ታዘጋጃላችሁ፡፡
- የጥናታችሁን የመጨረሻ ስራ በአጻጻፉ ቀርጽ መሰረት በትክክል ትጽፋላችሁ፡፡

ሁለቱን የመጀመሪያዎችን እና አራተኛውን አላማ ስንመለከት “የመጨረሻ ስራ” የሚል አሻሚ ሀረግ እናገኛለን፡፡ “የመጨረሻ ስራ” ምንድን ነው? የተጠናቀቀ ስራ ወይስ? በግልጽ የሚታወቅ ነገር የለውም፡፡ ሶስተኛው አላማ ደግሞ የግልጽነት ችግር አለበት፤ ይኸውም የጥናት ንድፍ በሚሰራበት ጊዜ ምርምሩ እየተከናወነ መሆኑን አያመለክትም? ወይም የምርምር ንድፍ የምርምሩ አካል አይደለም? የሚሉ መሰረታዊ ጥያቄዎችን ማስነሳቱ አይቀርም፡፡

በሌላም በኩል “የጥናታችሁን ንድፍ እና የጥናታችሁን የመጨረሻ ስራ” የሚሉት ሀረጎች የትኛውን ጥናት? የመመረቂያውን ጽሁፍ ወይስ ኮርሱን ለማሟላት የሚሰራውን ስራ? የሚሉ ጥያቄዎች በተማሪዎች አእምሮ ውስጥ መጫሩ አይቀርም፡፡ አንድን አላማ አብዛኛው ተማሪዎች ሲመለከቱትና ሲያነቡት ተመሳሳይ መልዕክት ካላስተላለፈላቸው አሻሚነት እንዳለው ማሰብ ይቻላል፡፡

## 3.4 የርቀት ትምህርት ሞጁሉ ይዘቶችን በተመለከተ

### 3.4.1 የርቀት ትምህርት ሞጁሉ አጠቃላይ ይዘት አደረጃጀት

በተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት ላይ በሰፊው እንደቀረበው ይዘቶች ሲደራጁ፡- በቅደም ተከተል፣ ለደረጃው በሚመጥን መልክ፣ በተገቢ መጠን እና በክፍል ወይም በምዕራፍ ተከፋፍለው ከሚታወቅ ወደ አማይታወቅ፣ ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከግልጽ ወደ ውስብስብ ወዘተ. ሊሆኑ ይገባል፡፡ በውስጡ የሚቀርቡትም ቁምነገሮች፣ ማስረጃዎች፣ መልመጃዎች፣ ወዘተ. የተቀረጹትን አላማዎች የሚያስፈጽሙ ሆነው መዘጋጀት አለባቸው፡፡ ከዚህ አኳያ “የምርምር ዘዴዎች” የሚለውን ሞጁል ስንመለከት የመጀመሪያው እና ሁለተኛው ምዕራፍ የያዟቸው ይዘቶች ተገቢ እና በቅደም ተከተል የተቀመጡ ቢሆንም ቀጥሎ የቀረቡት ግን ቅደም ተከተላቸውን ያልጠበቁ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች የምርምሩ ርዕሰ ጉዳይ ምንድን ነው? እንዴትስ ይመረጣል? የሚሉትና የጥናት ንድፍ ምንነት እንዲሁም አዘገጃጀትን በተመለከተ ሳይማሩ ወደ ተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት እንዲሸጋገሩ ተደርገዋል፡፡ በተጨማሪም እነዚህን ርዕሰ ጉዳዮች በተመለከተ ሞጁሉ በቂ ጊዜ ሰጥቶ የንድፈ ሀሳብ እውቀት እንዲያገኙ እና በተግባርም እንዲለማመዱ አላደረገም፡፡

ተማሪዎች ከዚህ ኮርስ ቀጥሎ የመመረቂያ ጽሁፋቸውን የሚያከናውኑ በመሆኑ የይዘቶች ቅደም ተከተልና ተገቢነት ወሳኝነት አለው፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን በልያንዳንዱ ይዘት ስር የሚሰጡ ተግባራትን እንዲለማመዱ የተለያዩ ሞዴል ስራዎችን በማሳየት እነሱም በተግባር እንዲሰሩ የተለያዩ መልጃዎችን ማቅረብ ተገቢ ነው፡፡

### 3.4.2 የርቀት ትምህርት ሞጁሉ ዝርዝር ይዘት አደረጃጀት

ምዕራፍ አንድ ውስጥ የተካተቱት ይዘቶች መርሃትምህርቱ ላይ በግልጽ የተቀመጡና ተገቢነት ያላቸውም ናቸው፡፡ ነገርግን እነሱን ለማብራራት የተዘረዘሩ ነጥቦች በሞጁሉ ላይ የሰፈሩ አላማዎችን በአግባቡ ለማሳካት አቅም የላቸውም፡፡ ለምሳሌ ምርምርን ለመበየን የተቀመጡ ነጥቦች ተማሪዎች ወደፊት ሲሰሯቸው ከሚገቡ ተግባራት ጋር የሚጣጣሙ አይደሉም፡፡ በቀረበው ብያኔ ውስጥ ምርምር ችግር ፈች ተግባራት የሚከናወኑበት ቁልፍ መሳሪያ መሆኑ አልተጠቀሰም፡፡ በሌላም በኩል የቀረቡ ይዘቶችን አንብበው የተረዱትን ነገር እንዲያንጸባርቁ የተለያዩ መልመጃዎች አልቀረቡላቸውም፡፡
በአላማዎች አቀራረጽ ግምገማ ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው በምዕራፍ ሁለት ውስጥ የተዘረዘሩት የመጨረሻዎቹ ሁለት አላማዎች ይላኩ ዘንድ የተደራጁ ይዘቶች የሏቸውም፡፡ በሞጁሉ ውስጥ የምርምር ርዕስ እንዴት እንደሚመረጥና ምርምር እንዴት እንደሚገመገም የሚያስተምሩ የመማር ተግባራትን በግልጽ ማግኘት አይቻልም፡፡
በሌላም በኩል ሌሎች የቀረቡ ምዕራፎች እንደ ምእራፍ አንድ ሁሉ በንድፈ ሀሳብ ደረጃ የተማሩትን ነገር ወደ ተግባር እንዲቀይሩ በሚያግዙ መልመጃዎች ወይም ክንውኖች አልታጀቡም፡፡ ከምዕራፍ አራት በስተቀር ሁሉም ምዕራፎች ትምህርቱ እንደተጠናቀቀ የማጠቃለያ መልመጃ ያቀረቡ ሲሆን ጥያቄዎቹም ተማሪው እንዲያብራራ ብቻ የሚጠይቁ ናቸው፡፡
ባጠቃላይ በሞጁሉ ውስጥ የቀረቡት ይዘቶች እንደ ክብደት ቅለታቸው በቅደም ተከተል ባለመደራጀታቸው የተማሪዎችን ተነሳሽነትና ፍላጎት ከፍ የማደረጋቸው ሁኔታ አነስተኛ ነው፡፡ በተጨማሪም የርቀት ትምህርት ሞጁል አደረጃጀትን ያልተከተለና በንድፈ ሀሳቦች የተጨናነቀ በመሆኑ ተማሪዎች የተወሰኑትን ነጥቦች አንብበው ቀም ብለው ለሳነበቡት ጉዳይ ራሳቸውን የሚመዝኑበት የቆምታ ጊዜ አልተፈጠረላቸውም፡፡ ከዚህም ሌላ ተገቢነት የሌላቸውና ከተማሪዎች አቅም በላይ የሆኑ ይዘቶች የተካተቱበት ሁኔታ ተንጸባርቋል፡፡

ለመጥቀስ ያህል የግርጌ እና የማጠቃለያ ማስታወሻ ( footnote and endnotes)፣ ዝኒ ከማሁ ወይም ከላይ እንደተጠቀሰው (Ibid, locit, opcit)፣ የልይይት ትንተና ዘዴ (ANOVA)፣ መደበኛ ልይይት (Standard deviation)፣ የዳግም ስኬት የልይይት ትንተና (repeated measures ANOVA) ወዘተ. ናቸው፡፡

## 3.5 የርቀት ትምህርት ሞጁሉ ቋንቋና አቀራረብ

### 3.5.1 ቋንቋውን በተመለከተ

ከዚህ በፊት ለመግለጽ እንደተሞከረው በዚህ ሞጁል ውስጥ ያለው የቋንቋ አጠቃቀም ሰዋሰዋዊ ስህተቱ ጎላ ያለ በመሆኑ ኣላማዎችን በግልጽ ለመረዳት አዳጋች እንደነበረ ታይቷል፡፡ በይዘቶች ውስጥ በቀረቡ ማብራሪያዎች ላይም ይህ ችግር ተንጸባርቋል፡፡

ምሳሌ 1፡-

> በተለያዩ ጊዜ የምርምር ምንነት የተጠቀሱትን ግንኙነቶች ውጤታማ ለማድረግ፣ በውጤቱም ተጠቃሚ ለመሆን ምርምር ምንድን ነው? ለሚለው ጥያቄ ተገቢ ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ (2002፡1)

ይህ ረዥም አረፍተ ነገር ግልጽነት የለውም፡፡ ምክንያቱም “ግንኙነት” እና “ውጤት” የሚሉት ቃላት በዚህ አገባብ ውስጥ ግር የሚያሰኙ ወይም ያለቦታቸው የገቡ ቃላት በመሆናቸው አረፍተ ነገሩን ስሜት እንዳይሰጥ አድርገውታል፡፡

ምሳሌ 2፡-

የመሰረታዊ ጥናትና ምርምር ዋና አላማ እውቀት ስፋትና ጥልቀት እንዲኖረው ማድረግ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ሳይንሳዊ ድንጋጌዎችን ለማመንጨት ያለው ሲሆን ስፋትና ጥልቀት ያለው ትንታኔ መሰረት ያደረገ የጥናትና ምርምር አይነት ነው፡፡ (2002፡6)

ሰዎች በአንድ በተወሰነ ነገር ትዕግስት በማጣታቸው ምክንያት ስራቸውን የሚተውት በርካታ ናቸው፡፡(2002፡3)

አረፍተ ነገሮቹ ምን ለማስተላለፍ እንደፈለጉ በቀላሉ ለማወቅ አስቸጋሪ ነው፡፡ በተጨማሪም ድግግሞሽ የበዛበት በመሆኑ ለማንበብም ያነቅፋል፡፡

ምሳሌ 3፡-

… ከዚህ በላይ ከተሰጠው ትርጉም አንጻር ለመረዳት የሚቻለውና ከእራሱ ከስያሜው የሚያመለክተው ነገር ቢኖር ተግባራዊ ምርምር የአካባቢ ችግሮች በማጥናትና ተግባራዊ መፍትሄ ለመፈለግ ኣላማ ያደረገ ተጨባጭ ውጤት የሚያስገኝ የምርምር አይነት ነው፡፡ (2002፡8)

እንደ Holmberg (1981) ገለጻ በርቀት ትምህርት ሞጁል አዘገጃጀት ውስጥ የቃላት መደጋገም እና የአረፍተ ነገር መርዘም የተነባቢነት ችግር ስለሚፈጥር በተማሪዎች ስኬት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ማሳደራቸው እንደማይቀር አስረድቷል፡፡ ከላይ እና ቀጥሎ የሚቀርቡትም አረፍተ ነገሮች ረዣዥም በመሆናቸው የባለቤትና የማሰሪያ አንቀጽ መጣጣም ችግር አለባቸው፡፡ ስለዚህም መልዕክታቸውን ለመረዳት አስቸጋሪ ነው፡፡

ምሳሌ 4‹-

“የተዛማጅ ጽሁፍ የሚባለው ምርምር ለማካሄድ ባለምነው ርዕሳችን ዙሪያ ተዛማጅነትና ተመሳሳይ አላማ ያላቸውን መረጃዎች፣ ሀሳቦች፣ ማብራሪያዎች፣ ወዘተ. የታተሙም ይሁኑ ያልታተሙ መዛግብት፣ ሰነዶች፣ ወዘተ. መምረጥ፣ ማሰስና መመዝገብ፣ እንዲሁም ከርዕሳችን አኳያ ሂሳዊ ትንታኔና ትችት በማካሄድ በሌሎች ያልታየውን አጉልቶና አንጥሮ ክፍተቱን በተጨባጭ መረጃ ማሳየት ይገባል፡፡” (2002፡43)

አረፍተ ነገሩ “የተዛማጅ ጽሁፍ የሚባለው…” ብሎ ከጀመረ በኋላ ያጠናቀቀው “በተጨባጭ መረጃ ማሳየት ይገባል፡፡” በሚል ሀረግ ነው፡፡ ይህም በጽሁፉ የቀረበው ነገር ብያኔ ወይስ ማብራሪያ? የሚል ጥያቄ ያስነሳል፡፡

ምሳሌ 5፡-

ሀ. ማንኛውም ተመራማሪ፣ የምርምር ውጤቶችን በሚተረጉሙበትና በሚያብራ
ሩበት ጊዜ ለአፍታ እንኳ መዘንጋት የሌለበት ነገር ምን ምን ናቸው? (2002፡ 90)

ለ. ምርምር አስተማማኝ ነው ከሚባልበት ነገሮች መካከል አንድ ምሳሌ በዝርዝር
አቅርቡ፡፡ (2002፡5)

እነዚህ አረፍተነገሮች በውስጣቸው የመደብ እና የቁጥር አለመስማማት ችግር ያለባቸው ናቸው፡፡ እንደዚህ እንደዚህ እያሉ ብዙ ችግሮችን ነቅሶ ማውጣት ይቻላል፡፡

### 3.5.2 የርቀት ትምህርት ሞጁሉ አቀራረብ

በሞጁሉ ውስጥ ያለው ቋንቋ ግልጽና ከሰዋሰው ግድፈት የጸዳ ከሆነ አቀራረቡም የተሸለ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ከዚህ በፊት እንደታየው አጻጻፉ በአብዛኛው በረጃጅም አረፍተ ነገሮች የተሞላ፣ ሰዋሰዋዊ ስህተት የበዛበት፣ ስርዓተ ነጥቦች ባግባቡ ያልተቀመጡበት፣ ድግግሞሽ የሚንጸባረቅበት በመሆኑ በአቀራረቡ ላይም አሉታዊ ተጽእኖ አሳድሯል፡፡ ይህም በመሆኑ ተማሪዎችን ለንባብ የማነሳሳት አቅሙ ዝቅተኛ ነው፡፡
ተማሪዎች ለርቀት ትምህርት ተብሎ የተዘጋጀውን ሞጁል በሚያነቡበት ጊዜ ልምዱንና እውቀቱን ከቀረቡት ይዘቶች ጋር አጣምሮ፣ በምሳሌዎችና በማስረጃዎች እያስደገፈ የሚያስተምራቸው አካል እንዳለ ሊሰማቸው ይገባል፡፡ የጽሁፎቹ ፍሰትም አንዱ ምዕራፍ ከሌሎች፣ አንዱ አንቀጽ ከሚቀጥለው፣ አንዱ አረፍተነገር ከሌላው አረፍተነገር እርስበርስ የተሳሰረና ፍሰታቸውን የጠበቁ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ነገርግን ለጥናት የተመረጠው ሞጁል ውስጥ የቀረቡ ይዘቶች ከተለያዩ መጽሀፎች እና ጽሁፎች ተቀንጭጭበው በማስታወሻ መልክ የቀረቡ እንጂ የሁለትዮሽ መስተጋብር የሚንጸባረቅባቸው፣ በተለያዩ ምሳሌዎችና ማስረጃዎች የተሞሉ አይደሉም፡፡ ለምሳሌ ከያለው እንዳወቀ (1997) "የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር" ከሚለው መጽሃፍ ምንጭ ሳይጠቀስባቸው በአብዛኛው የተወሰዱ ናቸው፡፡ ለምሳሌ በሞጁሉ ከገጽ 63 ጀምሮ ያለው ጽሁፍ ከያለው እንዳወቀ (1997) ከገጽ 93-94 "በጽሁፍ ውስጥ የተዛማጅ ጽሁፍ ምንጭ አጠቃቀስ" ከሚለው ንዑስ ርእሰ-ጉዳይ የተቀገለበጠ ነው፡፡

በተጨማሪም አቀራረቡ የይዘት ቅደም ተከተል እንደሌለው በሞጁሉ አጠቃላይ የይዘት አደረጃጀት ላይ በግልጽ ተነስቷል፡፡ በተጨማሪም ብዛት ያላቸው ይዘቶች ቢጋራቸው ወይም መንደርደሪያ አረፍተ ነገሮች ብቻ ተቀምጦላቸው የያለው እንዳወቀን (1997) "የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር" የሚለውን መጽሃፍ እንዲያነቡ የሚጠይቁ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡-

- የዋቢ ምንጮች አጠቃቀስ
- መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች እና
- ናሙና የሚሉት ናቸው፡፡

በሌላም በኩል ደግሞ ርዕሰ ጉዳያቸው ተቀምጦ ምንም ማብራሪያ ያልተሰጣቸው እና ዋቤ ጽሁፎችን እንኳ እንዲያነቡ ሳይጠቆሙ ጽንሰሀሳባቸው እንዲሁ ተድበስብሰው ያለፉም ይዘቶች አሉ፡፡ ለምሳሌ፡-

- ተለዋዋጮች
- መረጃ እንዴት ይተነተናል? እና
- የምርምር ንድፍ ናቸው፡፡

ከዚህም አልፎ አብዛኛው ጽሁፍ የትየባ እና የስርአተ ነጥብ በአግባቡ ያለመስፈር ችግር በሰፊው ይንጸባረቅበታል፡፡ ከዚህ በፊት የቀረቡት ምሳሌዎች ላይ ያለው የፊደል ስህተት እንዳለ ሆኖ ሌሎችንም ማስረጃዎች መጥቀስ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ፡-

ሀ. ምርምርን ምርምር የሚያሰኘው ከሌሎች መሀል(መሰል ለማለት)
እንቅስቃሴዎች የሚለየው የራሱ መገለጫዎች አሉት፡፡ (2002፡2)

ለ. አንድ ተመራማሪ ምርምር ለማካሄድ በሚያስብበት ወቅት ከዚህ በታች

የተገለጹትን በቅም (በቅደም ስማስት) ተከተል ማከናወን ይኖርበታል፡፡
(2002፡4)

ሐ. በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የምርምርን ምንነት & ( የስጠሳ ሰረዝ ምልክት ወይም እና ስማስት) የምርምርን ባህሪያት እና የምርምርን አከፋፈል በዝርዝር ስማየት ተሞክሯል፡፡ (2002፡6)

ሠ. የተዛማጅ ጽሁፍ ክለሳ ወይም ክለሳ ድርሳናት፣ (ያስቦታው የገባ ስርዓተ ነጥብ) በምርምር ስራ ውስጥ ከፍተኛ ጠቀሜታዎች ይሰጣል (ይሰጣሉ ስማስት)፡፡(2002፡45)

ሰ. ባጠቃላይ ሳንባቢያን፣(ያስቦታው የገባ ስርዓተ ነጥብ) በተመረጥነው (በተመረጠው ስማስት) የጥናት ርዕስ… ጠንካረና (ጠንካራ ስማስት)…
(2002፡45)

ረ. ከዚህ ሌሳ፣ (ያስቦታው የገባ ስርዓተ ነጥብ) አንዳንድ ረጃጅም ስሞች፣ ሀረጎችና ስያሜዎች በተደጋጋሚ በጥናቱ የሚያገለግሉን ሲሆኑ (ሲሆን ስማስት)፣ ወጥ የአፅርዖተ (የአጽህሮተ ስማስት) ቃሳት አጻጻፍ በመጠቀም፣ (ያስቦታው የገባ ስርዓተ ነጥብ) በዚሁ (ከዚሁ ስማስት) ከቃሳት ፍቺ ቀጥሎ ስአንባቢያን ማስተዋወቅ ይገባል፡፡(2002፡78)

# IV. ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳቦች

## 4.1 ማጠቃለያ

የጥናቱ አሳማ ይሳካ ዘንድ የቀረቡት ሶስት የምርምር ጥያቄዎችን ለመመለስ በተደረገው ጥረት የሚከተሉት ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡

ስጥናት የተመረጠው ሞጁል ከውጭ ሽፋኑ ጀምሮ ተማሪው ትምህርቱን ከመጀመረ በፊት ማከናወን ያለበትን የተለያዩ ተግባራት ያሳሳወቀ ብቻም ሳይሆን አጠቃሳይ መግቢያም የሌለው ነው፡፡ በተጨማሪም አብዛኛው ዝርዝር የምዕራፍ መግቢያዎች የትምህርቱን ዋና ዋና ርዕስ ጉዳዮች የሚያስቀምጡ እንጂ ያለፈውን ምዕራፍ ከቀጣዩ ጋር እያስተሳሰረ ተማሪዎችን የሚያነሳሱ አይደለም፡፡
አጠቃሳይም ሆነ ዝርዝር አሳማዎች አቀጣጫ የሚያሳዩ መሪ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ አጠቃሳይ አሳማ ተማሪዎች ወደ መጨረሻው ውጤት ስመድረስ ይችሉ ዘንድ ዛሬ ሳይ ቆመው ነገን የሚያዩበት መነጽር ነው፡፡ ነገር ግን ሞጁሉ ይህን ትልቅ ቁምነገር በውስጡ ባለማካተቱ በጥናቱ ውስጥ እንደ ሰፊ ክፍተት ታይቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ተማሪዎች ኮርሱን ተምረው ሲያጠናቅቁ ምን ሲያደርጉ እንደሚችሉ ባሳወቁበት ሁኔታ ወደ ትምህርቱ እንደገቡ ስመረዳት ተችሏል፡፡ በሌሳም በኩል ዝርዝር አሳማዎች በአብዛኛው ግልጽነት የጎደሳቸው፣ ተተግባሪነት የሌሳቸውና ሰዋሰዋዊ ግድፈት የበዛባቸው ናቸው፡፡ ከዚህም ሌሳ አሳማዎች በግልጽ ተቀምጠው ዝርዝር ማብራሪያዎች ባግባቡ ያልቀረቡበት ነው፡፡
በኮርሱ ውስጥ የቀረቡት አጠቃሳይ ይዘቶች በመርሃ ትምህርቱ መሰረት ቅደም ተከተሳቸውን ያልጠበቁ እና መሰረታዊ የሆኑ የምርምር ጽንሰ ሀሳቦችን ከእነማብራሪያቸው ያሳካተቱ ናቸው፡፡ የጥናቱ ውጤትም እንደሚያመለክተው ይዘቶቹ በመልመጃዎች፣ በተለያዩ ልምዶችና ማስረጃዎች ባለመደገፋቸው ተማሪዎችን በርቀት ስማስተማር የማስቻል አቅማቸው ዝቅተኛ ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም ከተማሪዎች አቅም በሳይ የሆኑ ስደረጃው የማይመጥኑ ይዘቶች፣ ስምሳሌ፡- የልይይት ትንተና ዘዴ (ANOVA)፣ መደበኛ ልይይት (Standard deviation)፣ የዳግም ስሌት የልይይት ትንተና (repeated

measures ANOVA) ወዘተ. መቀፈባቸው ተማሪዎችን ያደናግራሉ እንጅ የኮርሱን ዕላማ የማሳካታቸው ሁኔታ እምባዛም ነው፡፡

በዕላማ አቀራረጽና በይዘት አደረጃጀት ላይ የታዩ ችግሮች በአቀራረቡ እና በቋንቋው ላይ ተጽእኖ ማሳደራቸው አልቀረም፡፡ ይኸውም ዕላማዎች ሲቀርቡም ሆነ ይዘቶች ሲብራሩ የተለያዩ ሰዋሰዋዊ ስህተቶች መኖራቸው ፣ አረፍተነገሮቹ ረጃጅም በመሆናቸው የባለቤትና የግስ አለመጣጣም ማስከተላቸው፣ በጽሁፉ ውስጥ ስርአተ ነጥቦች ባግባቡ አለመግባታቸው፣ ይዘቶች በቅደም ተከተል አለመስፈራቸው እና የቀረቡ ይዘቶች ከተለያዩ መጽሀፎች እና ጽሁፎች ተቀነጫጭበው በማስታወሻ መልክ መስፈራቸው እና የሁለትዮሽ መስተጋብር የሌላቸው መሆኑ በአቀራረቡ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አሳድሯል፡፡
በመጨረሻም ለጥናት በተመረጠው ሞጁል ላይ የተፈጠሩት ችግሮች የርቀት ትምህርትን ለሚያስተምሩ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በዝግጅት ጊዜ፣ ከዝግጅት በኋላ እና በአተገባበር ደረጃ እነዚህን ነገሮች ለማስወገድ እና የትምህርቱን ጥራት ለመጠበቅ እንዲቻል ከዚህ ቀጥሎ የተለያዩ የመፍትሄ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

## 4.2 የመፍትሄ ሀሳቦች

የርቀት ትምህርት ከመደበኛው የፊት ለፊት የመማር ማስተማር ሂደት ወጣ ያለ፣ ግለሰባዊ ተግባራትን በከፍተኛ ሁኔታ የሚጠይቅ እና ተማሪው ተዘጋጅቶ በሚሰጠው ሞጁል አማካኝነት ራሱን እያገዘ ትምህርት የሚያገኝበት በመሆኑ ከፍተኛ ጥንቃቄ ተደርጎበት ትምህርቱ ሊሰጥ ይገባል፡፡ ሞጁሉ ሲዘጋጅ ከመደበኛው የመማሪያ መጽሀፎች በተለየ መልኩ የሁለትዮሽ መስተጋብር እንዲኖረው ተደርጎ፡- ዕላማው፣ የይዘት አደረጃጀቱ፣ ቋንቋውና አቀራረቡ ከዚህ ቀጥሎ በሚሰፍሩት ዋና ዋና ነጥቦች ላይ ቢያተኩር ውጤታማነቱ የጎላ ይሆናል፡፡
ተማሪው ወደ ዋናው ትምህርት ዘልቆ ከመግባቱ በፊት ምን ምን ተግባራትን ማከናወን እንዳለበት፣ በውስጡ የሚገኙ ይዘቶች ምን እንደሚመስሉ፣ ኮርሱን ሲያጠናቅቅ ከእሱ ልምድና ገጠመኝ ጋር አጣምሮ በትምህርት ላይ እያለም ሆነ ወደ ስራ ሲሰማራ ሊሰራበት የሚችለውን ነገር በአጠቃላይ መግቢያው ላይ ማመላከት ያስፈልጋል፡፡ ዝርዝር መግቢያዎችም ያለፈውን ምዕራፍ ከሚመጣው ጋር እያስተሳሰረ ተማሪዎች ወደ እለቱ ትምህርት እንዲገቡ የሚያነሳሱ ሆነው ቢሰፍሩ የተሸለ ነው፡፡
ተማሪው መነሻ እና መድረሻውን እንዲያውቅ፡- ትምህርቱን የሚማረው ለምንድን ነው? ኮርሱን ሲያጠናቅቅ በተማረው ነገር ምን ምን ነገሮችን ያከናውናል? የሚሉትን መሰረታዊ ጥያቄዎች በግልጽና በማያሻማ ሁኔታ በአጠቃላይ ዕላማው ላይ መመለስ አለባቸው፡፡ የየምእራፎቹ ዕላማዎችም በቀላሉ ሊለኩና ሊተገበሩ የሚችሉ፣ ግልጽና የማያሻሙ፣ ከሰዋሰው ግድፈት የራቁ እና በጥሩ የቋንቋ አጠቃቀም የተጻፉ ቢሆኑ ውጤታማነታቸው ከፍ ይላል፡፡
ይዘቶች ሲደራጁ፡- በቅደም ተከተል፣ ለደረጃው በሚመጥን መልክ፣ በተገቢ መጠን እና በክፍል ወይም በምዕራፍ ተከፋፍለው ከሚታወቅ ወደ እማይታወቅ፣ ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከግልጽ ወደ ውስብስብ ወዘተ. ቢሆኑ በቀላሉ የቀረበውን ዕላማ ለማሳካት ይረዳል፡፡
ተማሪዎች ለርቀት ትምህርት ተብሎ የተዘጋጀውን ሞጁል በሚያነቡበት ጊዜ ልምዱንና እውቀቱን ከቀረቡት ይዘቶች ጋር አጣምሮ፣ በምሳሌዎችና በማስረጃዎች እያስደገፈ የሚያስተምሩቸው አካል እንዳለ እንዲሰማቸው አድርጎ ማቀረብ የማንበብ ፍላጎትንና ተነሳሽነትን ይጨምራል ብሎ አጥኝው ያምናል፡፡ የጽሁፎቹ ፍሰትም አንዱ ምዕራፍ ከሌሎች፣ አንዱ አንቀጽ ከሚቀጥለው፣ አንዱ አረፍተነገር ከሌላው አረፍተነገር እርስበርስ የተሳሰረ ቢሆኑ ተነባቢነታቸው ይጨምራል፡፡

**ዋቢ ጽሁፎች**

ያለው እንዳወቀ። (1997)። **የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር**። አዲስ አበባ፡- **አልፋ አታሚዎች**።

Allwright, R. (1981) ‘‘What do we want teaching material for?” **ELT Journal.** Vol.36,No. 5-18.

Cunningsworth, A. (1984) **Evaluating and Selecting EFL Teaching Materials**. Oxford: Heineman.

Eshetu Wencheko (2006) “Sharing Experience in distance Education”. Retrieved from http://www.aau.edu.et/strategicplanning/conference1/resources/experiencedistancestudies-eshetuwoncheko.pdf

Tony, D. (1983). **Administration of Distance Teaching Institutions**. Cambridge: U.K. International extension college.

Graves, K. (1996). **Teachers as Course Developers**. Cambridge: CUP.

Holmberg, B. (1981). **Status and Trends of Distance Education**. New York: Nichols Publishing Company

Hutchinson,T. and A. Waters (1987). **English for Specific Purposes**. CUP.

McDonough, J. and C. Shaw (1993). Materials and Methods in ELT: A Teacher’s Guide. Oxford: Blackwell.

Nuttal, C. (1996). **Teaching Reading Skills in a Foreign Language**. Oxford: Heineman.

Richards,J and T. Rodgers, (2001). **Approaches and Methods in Language Teaching**. 2nd edition. Cambridge: CUP.

Rowntree, D. (1981). **A Dictionary of Education**. London: Harper and Row Publishers.

Smith, K. (1999). “Report to the Distance Education Evaluation Task Force: Distance Education Best Practices and Problems North Carolina A & T State University”. Accessed from http://qed.ncat.edu/ir&p/report.htm.